# Learning by Ear 2013

**"መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" – "መዘዙን መቀበል"**

EPISODE 21: **አዲስ ነዋሪ**

**AUTHOR: James Muhando**
**EDITORS: Friederike Müller, Maja Braun, Madelaine Meier**
**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: ሰብለ OFFICE**

- **ሰብለ (F, 50)**
- **ዳንኤል (M, 16)**

**SCENE 2: BREAK TIME AT BONGO ACADEMY**

- **አልማዝ (F, 16)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **ትዕግስት (F, 16)**

**SCENE 3: YOUTH CENTRE**

- **አልማዝ (F, 16)**
- **ንጉሴ (M, 16)**

**SCENE 4: ብሩክ LEAVES HOSPITAL**

- **ሉሊት (F, 40)**
- **SHOUTING DRIVER (M, 30s)**
- **ብሩክ (M, 8)**

- ቅዱስ **(M, 8)**
- ምህረት **(F, 15)**

## INTRO

## 1. NARRATOR:

**ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤  ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ  "መዘዙን መቀበል" የተሰኘዉ ሁለተኛ ዙር ድራማ ሲሆን ዘግየት ብሎ  ለታዳጊ ወጣቶቹ ነገሮች እየከበዱ ሄደዋል፡፡ ትዕግስት በእድሜ ብዙ ወደ ሚበልጣት ወንድ ጓደኛዋ፣ ምኞቴ፣ ጋር ጠቅልላ ከገባች በኋላ  መጀመሪያ አካባቢ የፍቅር ይመስል የነበረው ግንኙነት ድንገት  ምኞቴ በመጥፎ ሲይዛትና ቤት ቆልፎባት  ሲያስቀምጣት ነገሩ ሁሉ ወደ ቅዠት ተለዉጦባታል፡፡ እንደ እድል ሆኖ ጓደኛዋ ምህረት እና የክፍል ጓደኞቿ ሊያድኗት መጥተዋል…:**

### 2. EPISODE 20, LINES 67 – 70:

<u>ምህረት</u>***:*** ትዕግስት! ደህና ነሽ?

***GIRLS/BOYS:*** ምን ሆነሽ ነዉ?/ ደህና ነሽ?/ትዕግስት!

<u>ትዕግስት:  </u>***(cries)*** ምህረት! መጣሽ!እንዴ  መጣሽ! አመሰግናለሁ፣ በእውነት አመሰግናለሁ!

<u>አልማዝ:</u> ፍጠኑ፣ ይዘናት እንውጣ፡፡

## 3. NARRATOR:

**በእዚህ መሀል የምህረት ታናሽ ወንድም ብሩክ ለሳንባ ነቀርሳ ህክምና ሐኪም ቤት ተኝቶ ነበር፡፡ የሳንባ በሽታው ያገኘው እሱ እና መንታ ወንድሙ ቅዱስ በጎረቤት ሀገር ላቦሪያ የማዕድን ስፍራ ላይ ሲሰሩ ነበር፡፡ እህታቸው ምህረት ግን በአዕምሮዋ ሌላ ነገር እየተመላለሰ ነዉ፡፡ ከትምህርት ቤት ተባሮ ከነበረዉና እንደገና ወደ ቦንጎ አካዳሚ እንዲመለስ ከተፈቀደለት የክፍል ጓደኛዋ ዳንኤል ቀደም ሲል አርግዛለች፡፡ ዳንኤል ወደ ትምህርት ቤት  ዳግም ሲመለስ ቅፅር ጊቢው ውስጥ  ተለቅ  ያለ አስገራሚ ነገር ነው የጠበቀው።፡:**

## 4. EPISODE 20, LINES 115 – 120:

ምህረት: ሃይ፣ ዳንኤል፣

ዳንኤል፡ እምም…ሃይ…ሜ…ምህረት? (…)

አልማዝ: እንዴት ነህ፣ ዳንኤል!

ዳንኤል: አልማዝ? እዚህ ምን ትሰሪያለሽ?

## 5. NARRATOR:

የልዉዉጥ ትምህርት መረሃ-ግብር ተካፋዩዋዋ አልማዝ ላቦሪያ ውስጥ የዳንኤል የሴት ጓደኛ ነበረች፡፡ አሁን እሷም ቦንጎ አካዳሚ ገብታለች፡፡ ዳንኤል ግራ በሚያጋባ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለው! እስቲ ዳንኤልን “አዲስ ነዋሪ” በተሰኘው የድራማው 21 ኛ ክፍል የርዕሰ መምህርቷ ቢሮ ውስጥ እናግኘው፣

## SCENE 1: ዳንኤል IN ርዕሰ መምህርት ሰብለ OFFICE

## 6. ATMO: ርዕሰ መምህርት ሰብለ OFFICE, BREAK TIME

**7.** ሰብለ: እሺ ዳንኤል ከትምህርት ቤት ከተባረርክበት ጊዜ አንስቶ ያንን ሁሉ ጊዜ እዚሁ ኪሲምባ ውስጥ ከአጎቴ ጋር ነዉ የቆየኹት ነው የምትለኝ?

**8.** ዳንኤል: **(hesitates)** እምም…አዎ፣ ርዕሰ መምህርት ሰብለ

**9.** ሰብለ: ቤተሰብህ ላቦሪያ ውስጥ እንዴት እንዳለ ታውቃለህ?

**10.** ዳንኤል: እናቴ ደህና ናት፡፡ ቤተሰቦቿ ጋር ሄዳለች እናም አባቴ …

**11.** ሰብለ: አባትህ ምን?

**12.** ዳንኤል: **(embarrassed**ማለት…እሱ ተይዟል.

**13.** ሰብለ: ምን? ለምን?

**14.** ዳንኤል: በገንዘብ ነክ ወንጀል ነው ብለዋል… **(sighs)** እና በማዕድን ስፍራው ህጻናትን ሲያሰራ ነበር

**15.** ሰብለ: **(shocked)** ምን? **(sighs)** ጥሩ፣ ለነገሩ አይመለከተኝም፡፡ የዓመቱ የትምህርት ቤት ክፍያ እስከተከፈለ ድረስ አባትህ ለፈጸመዉ ተግባር አንተ ትምህርትን እንድታቋርጥ የሚደረግበት ምክንያት አይታየኝም፡፡ **(serious tone)** ከደብዳቤው እንደተረዳኸው የትምህርት ቤቱ ስነ-ስርዓት ኮሚቴ ተመልሰህ እንድትገባ ፈቅዷል፤

***KW BEGIN***

**16.** ዳንኤል: አመሰግናለሁ፣ እትዬ ሰብለ፤

**17.** ሰብለ: **(continues)** ሆኖም የሰራኸው ስራ በጣም የተሳሳተ እና ግብረገብነት የጎደለው ተግባር ነዉ፡፡ በቦንጎ አካዳሚ እንዲህ አይነቱ ባህሪ በቸልታ የሚታለፍ አይደለም፡፡ ትምህርት ቤቱ በየትኛውም አይነት ጸታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ተማሪዎች እንዲሳተፉ ፈጽሞ አይፈቅድም፡፡

**18.** ዳንኤል: ይቅርታ፣ እትዬ

***KW END***

**19.** ሰብለ: ዳንኤል፣ እዚህ መቆየት ከፈለግህ መስፈርቶቻችንን ሁሉ ማሟላት አለብህ፡፡ አንደኛ፤፡- ከየትኛዋም ሴት አጠገብ በድብቅም ሆነ በግልጽ የትም ቦታ ላይህ አልፈልግም፡፡ ሁለተኛ፤፡- ለስድስት ወራት በማስጠንቀቂያ እና በክትትል ትቆያለህ፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ምንም አይነት ስህተት ብትሰራ፣ የፈለገውን ያህል ትንሽ ቢሆን፣ ከነአካቴው ትባረራለህ! እናም በመጨረሻ፤ አሁን ለሰራኸው ስራ መቀጣት ይኖርብሃል፤ ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት በተማሪዎች መኖሪያ አካባቢ ያለውን የአበባ እርሻ ትንከባከባለህ፡፡ ገባህ?

**20.** ዳንኤል: ገብቶኛል  አትዬ ሰብለ

**21.** ሰብለ: አሁን፣ የአንተ እና የምህረት ቤተሰቦች የልጃችሁን ጉዳይ በተመለከተ እንዴት እንደሚትፈቱት፤ ማወቁ  እሱ የእኔ ጉዳይ  አይደለም። ግን ህጻኑን የመሸከም ኃላፊነቱ የምህረት ቢሆንም አንተም ኃላፊነቶች እንዳሉብህ ላሳውቅህ እፈልጋለሁ። ስለእነዚህ ጉዳዮች ለመማር አልማዝ በበጎ ፈቃደኝነት ወደምትሰራበት የታዳጊ ወጣቶች የአቻ ለአቻ ምክክር ማዕከል ትሄዳለህ።

**22.** ዳንኤል: አይሆንም! እባክዎን አትዬ ሰብለ፣ አልማዝ የአቻ ለአቻ አማካሪዬ ልትሆን አትችልም!

**23.** ሰብለ: አትጨነቅ። ስለ እዛ አልማዝ ነግራኛለች። እሷም አላበደችም አንተን የምታማክረዉ ። ወጣት አባቶች እና ልምዶቻቸውን የሚያካፍሉ ወንዶችን ትቀላቀላለህ፡ .

**24.** ዳንኤል: **(reluctantly)** እሺ፣ መምህርት።

**25.** ሰብለ: እሺ ዳንኤል፤ በኋላ ክፍል ውስጥ አገኝሀለሁ ። አሁን ትዕግስትን ጥራልኝ።

**26. SFX: STEPS ዳንኤል, DOOR OPENING**

**27. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 2: BREAK TIME AT BONGO**

**28. ATMO: BONGO ACADEMY, BREAK TIME, EXTERIOR**

***KW BEGIN***

**29.** አልማዝ: እሺ፣ ምህረት! ትናንትና አስደሳች ጊዜ ነበር! የትምህርት ቤታችሁን መዝሙር በጣም ነው የወደድኩት!**(sings the school anthem wrongly)** እንታገላለን እንዘምራለን /የትኛውንም ነገር እናደርጋለን /ካደናቀፍከን /ከመንገዳችን እናስወግድሀለን/ ቦንጎ የራሱን ይከላከላል! አይደለም!

**30.** ምህረት: **(laughs)** አይደለም፣ አይደለም፣ አልማዝ፣ እንደዛ አይደለም፥

**31.** አልማዝ:ምን? ትናንትና የዘመርነው እንደዚያ ነው።

**32.** ምህረት: **(chuckles)** አልማዝ፣ ቀልደኛ ነሽ። መዝሙሩ ግን እንዲህ ነዉ የሚለው**(sings)** እየተዋጋን እናሸንፋለን/ንጉሱ ማን እንደሆን እናሳያለን /መንገዳችን ላይ አትጋረጥ /አደራ እንዳትመላለጥ /በቦንጎ ፈጽሞ ብቸኝነት የለም /ምክንያቱም ቦንጎ የራሱን ይከላከላል።

**33.** አልማዝ: ልክ ነው፣ ምንም ይሁን። ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት ትናንትና ነው።

**34.** ምህረት **AND** አልማዝ **LAUGH**

***KW END***

**35.** አልማዝ: ተመልከች፣ ምህረት፣ ትዕግስት መጣች።

**36. SFX: FOOTSTEPS APPROACH**

**37.** ትዕግስት: **(as she approaches)** ሃይ፣ ምህረት፣ አልማዝ-እንዴ! እናንተ ሁለታችሁን ያስደሰታችሁ ነገር ምንድን ነው?

**38.** ምህረት: ምንም- የዝውውሯ ተማሪያችን አልማዝን ስለ ትምህርት ቤታችን ልምዶች እያስተማርኳት ነው፡፡

**39. THEY LAUGH**

**40.** አልማዝ: **(serious again)** ሄይ ትዕግስት፣ ርዕሰ መምህርት ሰብለ ምን አለች?

**41.** ትዕግስት: **(thoughtful)** ስለ ብዙ ነገር፡፡ በረዥሙ ተነጋገርን፡፡ እናቴንም ጠርታታለች፡፡

***KW BEGIN***

**42.** ምህረት: እና፣ ምኞቴ ጋር ጠቅልለሽ ገብተሽ እንደነበር ለርዕሰ መምህርት ሰብለ ነገርሻቸው?

**43.** ትዕግስት: ልነግራት ባልፈልግም…ቀድማኝ አውቃለች፡፡ በሀሰት በእስር ማቆየት ወንጀል ፖሊስ ምኞቴን በቁጥጥር ስር አውሎታል፡፡ እዚያ ሄጄ ቃሌን መስጠት አለብኝ፡ .

**44.** አልማዝ: ጥሩ! በሰራው ስራ ስለሚቀጣ ደስ ብሎኛል፡፡

**45.** ምህረት: እኔም፡፡ ግን መምህርት ሰብለ አንቺን ከትምህርት ቤት አግዳሽ ነበር እንዴ ትዕግስት?

**46.** ትዕግስት: አይ! በጣም ገርሞኝ ነው፣ ደግሜ ይህንን ትምህርት ቤት የማየው አልመሰለኝም ነበር! ለነገሩ እናቴን ማገዱሳያስደስታት የቀረ አልመሰለኝም

**47.** ምህረት/አልማዝ: ምን?

**48.** ትዕግስት: ስለ ልጆች ኃላፊነት መውሰድ እና የመሳሰሉ ነገሮችን በስልክ ስታናግራት ሳትሰሙኣት አልቀራችሁም! ለነገሩ ርዕሰ መምህርት ሰብለ የምትገርም ናት። ለእናቴ ላዝንላት ምን ቀረኝ፡፡

***KW END***

**49.** አልማዝ **AND** ምህረት **LAUGH**

**50.** ትዕግስት: የምሬን ነው፣ እናንተ ባትመጡልኝ ኖሮ ምን ይከሰትብኝ እንደነበር አላውቅም። እኔን ለማዳን ተማሪዎችን በመቀስቀሳችሁ አመሰግናለሁ። እና አልማዝ ሌሊቱን ክፍልሽ ውስጥ ስላሳደርሽኝም አመሰግናለሁ፡ **(serious again)**

**51.** አልማዝ: በፈለግሽው ጊዜ ተመልሰሽ ነይ።

**52.** ትዕግስት: ያ አያስፈልግም። ከአሁን ጀምሮ በቦንጎ አካዳሚ እኖራለሁ!

**53.** ምህረት/አልማዝ: ምን? ሲገርም! !

**54.** ትዕግስት: አዎ፤ ቢያንስ ለሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት። በትክክለኛ ቁጥጥር እና ክትትል ስር መሆኔን ለማረጋገጥ ርዕሰ መምህርት ሰብለ እና እናቴ የተነጋገሩበት ነው። .

***KW BEGIN***

**55.** ምህረት: ጥሩ መፍትሄ ይመስላል።

**56.** ትዕግስት: እኔም እንደዚያ ይመስለኛል። ምህረት...ስሚ አንድ ነገር ልነግርሽ እፈልጋለሁ። ስላደረኩብሽ ነገር ሁሉ በእውነት አዝኛለሁ።

**57.** ምህረት: ማለት ወደ ዶክተር ዚቶ ሄጄ ማስወረድ እንድሞክር መንገርሽን ነው? ስሚ- ምንም አይደለም፣ ትዕግስት ያን እንርሳው። አንቺ ራስሽ በጣም ከባድ ጊዜ አሳልፈሻል...

**58.** ትዕግስት: እሱ አይደለም... ስለ አንቺ እና ስለ ዳንኤል ለመምህርት ሰብለ የነገርኳት እኔው ነበርኩ።

**59.** ምህረት: **(not surprised)** ውይ፣ ያንን? ገና ድሮ ነው የሰማሁት ባክሽ። ንጉሤነዉ የነገረኝ።

**60.** ትዕግስት: **(surprised)** ምን?

**61.** ምህረት: ርዕሰ መምህርት ሰብለ ባይነገራትም እንኳ አነፍንፋ ትደርስበት ነበር እሺ፣ እህ አሁን ስለመባረሬ ምንም ነገር ማሰብ አልፈልግም -ግን ከዚያ ሁሉ በኋላ ተመልሼ  ወደ ትምህርት ቤት መምጣት ችያለሁ። በስተመጨረሻ ሁሉም ነገር በሰላም ተጠናቆአል ማለት ነዉ

**62.** ትዕግስት: ምህረት፣ በእውነት ይቅርታ። በእርግዝናሽ በኩል ማንኛውም አይነት እርዳታ ቢያስፈልግሽ ልረዳሽ ቃል እገባለሁ።

**63.** ምህረት: አመሰግናለሁ፣ ትዕግስት ግን በቀጥታ ልጁን ሆድሽ ውስጥ ልትይዢልኝ ፣ አትችይም? ትችያለሽ…

**64. THEY LAUGH**

***KW END***

**65. SFX: SCHOOL BELL RINGS**

**66.** አልማዝ: እናንተ ልጆች፣ ወደ ክፍል እንግባ!

**67.** ምህረት: እሺ። በነገራችን ላይ አልማዝ ዛሬ ከሰዓት ወደ ወጣቶች ማዕከል መምጣት ስለማልችል ይቅርታ። ለ ሌላ ጊዜ ልናሸጋሸገው  እንችላለን? በስተመጨረሻ ወንድሜ ከሆስፒታል ስለሚወጣ ሄደን ማምጣት አለብን።

**68.** አልማዝ: ምንም  ችግር የለም፣ ምህረት።

**69. MUSICAL INTERLUDE**

## SCENE 3: አልማዝ AND ንጉሴ AT THE YOUTH CENTRE

### 70. ATMO: TRAFFIC HEARD FROM OUTSIDE, PEOPLE TALKING IN THE BACKGROUND (HEARD THROUGH DOOR)

### 71. SFX: DOOR CLOSED

**72.** አልማዝ: ንጉሜ፣ ወደ ወጣት ማዕከሉ እንኳን ደህና መጣህ። ሁላችንም አንድ ላይ ለውይይት ከመሰባሰባችን በፊት እኔ እና አንተ ብቻ ቢሮ ውስጥ ትንሽ ማዉራት እንችላለን? ይሆናል?

**73.** ንጉሴ: ይቻላል፣ አልማዝ።

**74.** አልማዝ: ና እንቀመጥ

### 75. SFX: TWO CHAIRS SCRAPING

**76.** አልማዝ: እንደሚታወቀው በዚህ ወጣት ማዕከል የአቻለአቻ ቡድን አማካሪ በመሆን በበጎ ፈቃደኝነት እሰራለሁ።

**77.** ንጉሴ: ኧረ- አልማዝ፣ ስለቋረጥኩሽ ይቅርታ፣ ግን የአቻ ለአቻ ቡድን አማካሪ ምን ማለት ነው?

**78.** አልማዝ: በተመሳሳይ እድሜ ያሉ ልጆች ችግር ውስጥ ሲገቡ ለእኩዮቹ ምክር መስጠት እንዲችል የሰለጠነ ሰው ማለት ነው።

***KW BEGIN***

**79.** ንጉሴ: ከሌሎች አማካሪዎች ለእኔ ምንም የተለየ አይመስልም።

**80.** አልማዝ: እውነቱን ለመናገር በጣም ይለያል። እዚህ ያለነው ሁላችንም ወጣቶች ስንሆን የየራሳችንን ልምድ እንከፋፈላለን። ምን ማድረግ እንዳለብን ማንም አይነግረንም። ታላቅ እህትህ አይደለሁም። የእድሜ እኩያህ ነኝ። አንተ ከምታውቀው በላይ አውቃለሁ ብዬም አልንጠራራም።

***KW END***

**81.** ንጉሴ: ስለ የእጽ ሱሰኝነት ችግሬ ከአንቺ ጋር እንድንነጋገር መምህርት ሰብለ ትፈልጋለች…ግን እኔን አልተመቸኝም። ማለቴ አንቺ…ማለቴ፣ ታውቂያለሽ…

**82.** አልማዝ: **(cuts in)** ሴት ነኝ? እንዲህ አይነቱን ጉዳይ ከተቃራኒ ጾታ አባል ጋር መወያየት ፈጽሞ እንደማይመች አውቃለሁ። ግን ልትነግረኝ የምትፈልገውን ማንኛውንም ነገር ከዚህ ክፍል እንደማይወጣ ቃል እገባልሃለሁ።

**83.** ንጉሴ: **(sighs)** እሺ! ምን ማወቅ ትፈልጊያለሽ?

**84.** አልማዝ: ማጨስ እና መጠጣት ለምን ጀመርክ?

***KW BEGIN***

**85.** ንጉሴ: አላውቅም። ግን አስደሳች ነገር መስሎኝ ይመስለኛል።|

**86.** አልማዝ እውነት?

***KW END***

**87.** ንጉሴ: ምንአልባት የጭንቀቴን መጠን ለመቀነስም ነበር።

**88.** አልማዝ: ተጨንቀህ ነበር? በ ምን ምክንያት?

***KW BEGIN***

**89.** ንጉሴ: ብዙ ነገሮች ምክንያት…

**90.** አልማዝ: ንጉሤ፣ ልታምነኝ ይገባል። እዚህ ጋር የምንወያየው ነገር መምህርት ሰብለ እንኳ እንደማትሰማው ነግሬሀለሁ። እሷ ማወቅ የምትፈልገው የእኛ ስብሰባ ላይ መገኘትህን እና ለውጥ ማሳየትህን ነው። ሌላ ዝርዝር አትፈልግም።

***KW END***

**91.** ንጉሴ: **(sighs)** እሺ ከዚያ። ስለሆነች ልጅም ተጨናንቄ ነበር…

**92. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 4: ብሩክ LEAVES HOSPITAL</u>**

**93. SFX: STREET ATMO, TRAFFIC**

**94.** ምህረት: ወንድሜ ብሩክ በመጨረሻ ከሆስፒታል ወጥተሀል! ምን ተሰማህ?

**95.** ብሩክ: ደስታ!

**96.** ቅዱስ: ደስ ይላል! አሁን ቀኑን ሙሉ መጫወት እንችላለን።

***KW BEGIN***

**97. SFX: CAR HOOTS, SCREECHES**

**98.** ሉሊት: **(screams)** ተጠንቀቅ፣ ቅዱስ! ወዲያ እና ወዲህ ሳትመለከት መንገዱ ላይ ምን ያስሮጥሀል? ወደ ሆስፒታል እንደገና ልትመልሰን ትፈልጋለህ?

**99. DRIVER:** **(shouts from a distance)** ሄይ! አንቺ ሴትዮ ልጆችሽን ጠብቂ!

**100. SFX: CAR DRIVES OFF**

**101.** ሉሊት: **(not serious)** ና ወደ እዚህ። እነዚህ መስማት የተሳናቸውን የጥንቸል ጆሮዎችህን መቆነጠጥ አለብኝ።

**102.** ቅዱስ **(laughs)** አው! አው! እማዬ፣ ያማል!

**103.** ምህረት/ብሩክ: **LAUGH**

**104.** ሉሊት**:** መንገድ ስለማቋረጥ ምን ተናግሪ ነበር?

**105.** ብሩክ አውቄአለሁ፣ እማዬ ወደ ሁለቱም አቅጣጫዎች መመልከት አለብኝ።

**106.** ምህረት: አይደለም፣ ብሩክ ሁለቱንም አቅጣጫ አይተህ ምንም አይነት መኪና እየመጣ አለመሆኑን ስታረጋግጥ ብቻ መንገዱን አቋርጥ

***KW END***

**107. SFX: MOBILE PHONE RINGS**

**108. SFX: BEEPS AS PHONE IS ANSWERED**

**109.** ሉሊት**:** ሄሎ? **(surprised, decidedly)** ለምለም**?** እንደው ግን አንቺ እንዴት እንዴት ብትደፍሪ ነው…ባለቤቴ እዚህ የለም፤ ስሚኝ፤ ሁለቱ ልጆቼ በራሳቸው ጥረት ከላቦሪያ እዚህ ከመጡበት ጊዜ አንስቶ በስልክ ላገኝሽ ሞክሬ ነበር! ሁሉንም ነገር ነግረውኛል! ከእዚህ ስትወስጂያቸው እንደምታሳድጊያቸው ቃል ብትገቢም አንቺ ግን በማዕድን ስፍራ ሸጥሻቸው…አታቋርጪኝ! ብሩክ ሞትዋል ማለት ይቻላል!…ምን አልሽ?…ላቦሪያ ፖሊስ ጣቢያ?… ማን ነው የተያዘው?…ካሳሁን? ማን ነው ካሳሁን?…ታውቂያለሽ ለምለም? ሁለታችሁም ወህኒ እንደምትበሰብሷት ተስፋ አደርጋለሁ። ምክንያቱም የእናንተትክክለኛ ቦታችሁ እዛ ነው! ልክ እንደ ወንድምሽ! ከዚህ በኋላ መቼም ቢሆን ደግመሽ በዚህ ቁጥር ለመደወል እንዳታስቢ!

**110. SFX: PHONE DISCONNECTS**

**111. ሉሊት:** **(clicks her tongue)**

**112. ምህረት:** ምንድን ነው እማዬ? የተናደድሽ ትመስያለሽ። .

**113. ሉሊት:** አክስትሽ ለምለም ነች። እርዳታ ፈልጋ ደወለች፣ እሷ እና ያ ካሳሁን የሚባል ሰውዬ በቁጥጥር ስር ውለዋል። እግዚአብሔር ይመስገን!

**114. ቅዱስ/ብሩክ:** **(whisper)** ካሳሁን? ካሳሁን? እሱ ነው!

**115. ምህረት:** ቆይ! ካሳሁን ነው ያልሽው? ከላቦሪያ?

**116. ሉሊት:** አዎ። እንደሱ ነው ያለችው፡

**117. ምህረት:** **(shocked)** የዳንኤል አባት መሆን አለበት።

**118. ሉሊት:** ማለት፤ ዳንኤል አንቺን እንደዛ ያደረገዉ…? ምን አይነት አውሬ ቤተሰቦች ናቸው!

**119. <u>OUTRO – NARRATOR:</u>**

እንዲህ ነው! የስልክ ጥሪው እና የለምለም እንዲሁም የካሳሁን በቁጥጥር ስር መዋል ለምህረት ብቻ ሳይሆን ለእናቷ እና ለሁለቱ ወንድሞቿም የሚያስደንቅ ዜና ነበር። አሁን የሰሙትን ነገር እንዲያጣጥሙት እዚሁ እንተዋቸው። በሌላ ጊዜ ሁሉንም በድጋሚ እናገኛቸዋለን። ያኔ ግን ጠብቃችሁ መከታተላችሁን እንዳትዘነጉ። ቀጣዩን ክፍል ድራማ ይዘን እንመለሳለን። የዛሬዉን ድራማ አለያም ከእዚህ በፊት ያመለጣችሁን በድጋሚ ለማድመጥ በድረ-ገጽ አድራሻችን **dw.de/lbe** ላይ ያገኙታል። ድራማዉን በግል መዝገቦ ላይም መገልበጥ ይችላሉ። በፌስ ቡክ ገጻችን ላይም ሊከታተሉን እንደሚችሉ አይዘንጉ። ጤና ይስጥልን!